## ከጁን 2021 ጀምሮ ለመዋዕለ ሕጻናት/ለኤስ.ኤፍ.ኡ. ቅናሽ የወላጆች ክፍያ

**መዋዕለ ሕጻናት**

**የዓመት ገቢያቸው ከ 592 167 kroner በታች ለሆኑ ቤተሰቦች ቅናሽ የወላጆች ክፍያ**

በአንድ ቤት ውስጥ የሚኖሩ ጠቅላላ ዓመታዊ ገቢያቸው ከ 592 167 kroner በታች የሆነ፣ ለመዋዕለ ሕጻናት ቅናሽ የወላጆች ክፍያ ለመክፈል ማመልከት ይችላሉ። ብዙ ልጆች ካሏችሁ ለእያንዳንዱ ልጅ ማመልከት እንዳለባችሁ አስታውሱ።

**የዓመት ገቢያቸው ከ 583 650 kroner በታች ለሆነ ቤተሰቦች ተጨማሪ ነጻ ዋና ጊዜ**

ነጻ ዋና ጊዜ ማለት ሕጻኑ በመዋዕለ ህጻናቱ ውስጥ በሳምንት የ 20 ሰዓታት ነጻ ቆይታ ያገኛል ማለት ነው። ይህን ነጻ ዋና ጊዜ ማግኘት የሚቻለው ልጅዎ ሁለት ዓመት በሚሞላበት ዓመት ውስጥ ከኦገስት ወር ጀምሮ ነው። ቅናሽ የወላጆች ክፍያ ለመክፈል የሚያመለክቱ ከሆነና የቤተሰብዎ ዓመታዊ ገቢ ከ 583 650 kroner በታች ከሆነ፣ በቀጥታ ነጻ ዋና ጊዜ ያገኛሉ።

**ኤስ.ኤፍ.ኡ.**

**የዓመት ገቢያቸው ከ 505 083 kroner በታች ለሆኑ ቤተሰቦች ቅናሽ የወላጆች ክፍያ**

በአንድ ቤት ውስጥ የሚኖሩ ጠቅላላ ዓመታዊ ገቢያቸው ከ 505 083 kroner በታች የሆነ፣ ለ ኤስ.ኤፍ.ኡ. ቅናሽ የወላጆች ክፍያ ለመክፈል ማመልከት ይችላሉ።

**የዓመት ገቢያቸው ከ 350 000 kroner በታች ለሆነ ቤተሰቦች ነጻ ኤስ.ኤፍ.ኡ. ለ1ኛ ክፍል**

ለ ኤስ.ኤፍ.ኡ. ቅናሽ የወላጆች ክፍያ ለመክፈል የሚያመለክቱ ከሆነ፣ እንዲሁም የቤተሰብዎ የዓመት ገቢ ከ 350 000 kroner በታች ሆኖ ልጅዎ 1ኛ ክፍል የሚሄድ ከሆነ በቀጥታ ነጻ ኤስ.ኤፍ.ኡ. ያገኛሉ።

### እንደዚህ ነው የሚያመለክቱት

በኤሌክትሮኒክ መንገድ ነው የሚያመለክቱት። ሕጋዊ የሆኑ ሰነዶችን አባሪ ያድርጉ። ለማመልከት በመታወቂያ መግቢያ በር (Bank ID, MinID, እና በመሳሰሉት) ነው የሚገቡት።

**የማመልከቻ ቅጹን እዚህ ላይ ያገኛሉ:**

www.bergen.kommune.no/redusert-foreldrebetaling

**ህጋዊ ሰነድ የሚባለው ምንድን ነው**

- ከህጻኑ ጋር በአንድ ቤት የሚኖሩ አዋቂዎች የ 2020 የግብር ሪፖርታቸውን ከማመልከቻው ጋር አባሪ ማድረግ አለባቸው
- ከግብር ሪፖርቱ አንጻር ገቢዎ ላይ ከፍተኛ ለውጥ ካለ፣ የመጨረሻዎቹን ሦስት ወራት የደሞዝ ወረቀት አባሪ ማድረግ ይችላሉ
- ጊዜያዊ የሥራ ስንብት ከተሰጠዎት፣ አሰሪዎ የሰጠዎትን ሰነድ አባሪ ማድረግ ይችላሉ
- ከብድር ካዝና እርዳታ እንዲያገኙ የተወሰነበት ደብዳቤ እና የተማሪ መታወቂያ ወረቀት
- የNAV ማህበራዊ ቢሮ ውሳኔ/የNAV ማህበራዊ ቢሮ ውሳኔ የተሻረበት ደብዳቤ
- ከNAV የእገዛ ውሳኔ በመጠባበቅ ላይ ካሉ፣ ይህንኑ በሰነድ ማረጋገጥ ይኖርቦታል
- አሁን ያለዎትን ገቢ የሚመለከቱ ሌሎች ሰነዶች

**እኔ የግብር ሪፖርት የለኝም**
ባለፈው ዓመት በኖርዌይ አገር ነዋሪ የነበሩ ሁሉ የግብር ሪፖርት ይኖራቸዋል። እናም ይህን ከማመልከቻው ጋር አባሪ ማድረግ አለባቸው። ለኖርዌይ አዲስ ከሆኑ እና የግብር ሪፖርት ከሌለዎት፣ የግዴታ በኖርዌይ ያለዎትን የመኖሪያ ፈቃድ ሰነድ አባሪ ማድረግ አለብዎት።

**ማመልከቻው የሚሰራው ከመቼ ጀምሮ ነው**
ለቅናሽ የወላጆች ክፍያ የሚላክ ማመልከቻ የሚሰራው ማመልከቻው ከደረሰ በኋላ ካለው ወር ጀምሮ ነው። ማመልከቻው ሲፈቀድ የውሳኔ ደብዳቤ ይላክሎታል።

**እኔ የማህበራዊ ዋስትና ቁጥር የለኝም/በኤሌክትሮኒክስ መንገድ ማመልከት አልችልም**
Kaigaten 4 የሚገኘውን የበርገን ኮሙነ የነዋሪዎች አገልግሎት መሥሪያ ቤት ያነጋግሩ። እዚያ በኤሌክትሮኒክስ መንገድ ለማመልከት፣ ወይም የማህበራዊ ዋስትና ቁጥር ከሌለዎት በእጅ ሞልተው እንዲያመለከቱ ያግዙዎታል። ለማመልከቻው አስፈላጊ የሆኑ ሰነዶችን ይዘው ይሂዱ። የነዋሪዎች አገልግሎት መሥሪያ ቤት ስልክ ቁጥር 55 56 55 56 ነው።

**ማሳሰቢያ! ለእያንዳንዱ የመዋዕለ ሕጻናት ዓመት እንደሚያመለክቱ ያስታውሱ!**
ለቅናሽ የወላጆች ክፍያ የሚላክ ማመልከቻ የሚሰራው ለአንድ ዓመት ነው። በኦገስት ውስጥ ቅናሽ ክፍያ ለማግኘት አዲስ ማመልከቻ ቢዘገይ በ ጁላይ ወር ውስጥ ማስገባት አለብዎት።